# በደቡብ ክልል መንግስት

# በፍትህ ቢሮ እና በሥር መዋቅር የሥራ ክፍሎችን የሚመሩ የሥራ ሀላፊዎች ምልመላና የውድድር አፈፃጸም መመሪያ ቁጥር 81/2017

መስከረም /2017 ዓ.ም

ሳውላ

## መግቢያ

የደቡብ ኢትዬጵያ ክልል ፍትሕ ቢሮ ራዕዩን እና ተልዕኮውን በብቃት ለማሳካት የሚያስችል የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ምደባ ለማድረግ የሕግ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የቢሮውን አገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የተሻለ የአመራር ብቃት ያለው የሥራ ክፍል ኃላፊ ለመመደብ የሚያስችል ሁሉን አቀፍ የማወዳደሪያ መስፈርት ማዘጋጀት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

**በቢሮው በየሥራ ክፍሉ የአገልግሎት ሰጪ ሠራተኛውን እና ለሥራ ክፍሉ የሰጡ ተግባራትን በህግና በአሠራር ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የሚመራና የሚያስተባብሩ ዳይሬክተሮች እና የሥራ ሂደት አስተባባሪዎችን የህግ ማዕቀፍ በመዘርጋት በፍትሐዊነት መልምሎ ለመመደብ አስፈላጊ በመሆኑ፤**

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ፍትህ ቢሮ በክልሉ የፍትህ ቢሮን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 12/2016 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 2 እና የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ባወጣው የዐቃቢያነ ህጎች መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 88/2016 አንቀጽ ----- ንዑስ አንቀጽ ----- ላይ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

## ጠቅላላ

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ፍትህ ቢሮ እና በሥር መዋቅሮች የሥራ ክፍሎችን የሚመሩ የሥራ ክፍል ኃላፊዎችን ለመመደብ የወጣ የምልመላና ውድድር አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 81/2017 ተብሎ ይጠቀሳል።

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ክልል"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ነው፤
2. **"ቢሮ"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ፍትህ ቢሮ ነው፤
3. **"አዋጅ"** ማለት **የክልሉ** ፍትህ ቢሮ **ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 12/2016 ነው እና እንደአስፈላጊነቱ የክልሉ አስተዳደር ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 32/2016 ያካትታል፤**
4. **"ደንብ"** ማለት **የክልሉ** ፍትህ ቢሮ ዐቃቢያነ ህግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 88/2016 ነው፤
5. **"መሥሪያ ቤት"** ማለት የክልሉ ፍትህ ቢሮ፣የዞን ፍትህ መምሪያ፣ የወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት ነው፤
6. **"የሥራ ክፍል"** ማለት የክልል ፍትሕ ቢሮ፣ በፍትህ ቢሮ ቋሚ ምድብ ፅህፈት ቤቶች፣ በዞን ፍትህ መምሪያ፣በወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት በመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ጥናት ወይም የተቋሙን አደረጃጀት፣ አሰራር፣ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ ማኑዋል በጥናት የተለዩ የሥራ ክፍሎችን ነው፤
7. **"ኃላፊ"** ማለት የክልሉ ፍትህ ቢሮ ኃላፊ፣ የዞን ፍትህ መምሪያ ኃላፊ፣የልዩ ወረዳ፣የወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት ሀላፊ ነው፤
8. **"የሥራ ክፍል ሀላፊ"** ማለት **በክልሉ** ፍትሕ ቢሮ፣ በዞን ፍትህ መምሪያ፣በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት በመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት ወይም በተቋሙ አደረጃጀትና አሰራር፣ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣ ማኑዋል በጥናት የተለዩ ዳሬክቶሬቶች፣ፅህፈት ቤቶች፣ስራ ሂደቶች፣ ዳይሬክቶሬቶች፣ የሥራ ክፍሎች

ላይ በዚህ መመሪያ መሠረት ተወዳድረውና አሸንፈው የሚመደብ የስራ ክፍል ኃላፊ ነው፤

9. **"አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ"** ማለት በሕግ ትምህርት ዘርፍ በዲፕሎማ እና ከዚያ በላይ ከተመረቀ በኋላ በዐቃቤ-ሕግነት፣ በዳኝነት፣በመደበኛ ፍርድ ቤት ሬጅስትራርነት፣በፍርድ አፍሰርነት፣በረዳት ዳኝነት፣በተከላካይ ጠበቃነት፣ በነገረ ፈጅነት፣ በጠበቃነት፣በሕግ ባለሙያነት(ኤክስፐርትነት)፣ በሕግ አማካሪነት ወይም በሕግ ትምህርት መምህርነት፣ በፍትህ ቢሮ ወይም በሥር መዋቅር ባሉት መስሪያ ቤቶች በኃላፊነት፣በፍትህ ቢሮ እና በስር መዋቅር አስቀድሞ ዐቃቤ ህግ የነበሩና ወደ ስነ ምግባር ኦፊሰርነት ተመድበዉ በመስራት የተገኘ ስራ ልምድ ሲሆን የቅድመ-ሥራ ላይ ስልጠና ቆይታ ጊዜንም ይጨምራል፤

10. **"በኃላፊነት ያገለገለ"** ማለት ተወዳዳሪው በህግ ትምህርት በዲፕሎማ ወይም ከዚያ በላይ ከተመረቀ በኋላ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ሀላፊነት ወይም በምትክል ቢሮ ኃላፊነት፤በዳይሬክቶሬት ዳይሬክተርነት ወይም በዞን ፍትህ መምሪያ፤በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር በመምሪያ እና በፍትህ ጽህፈት ቤት ሀላፊነት እንዲሁም በዞን፣ በወረዳም ሆነ በከተማ አስተዳደር ደረጃ በሥራ ሂደት አስተባባሪነት፣ በየደረጃው ባሉት መደበኛ ፍርድ ቤቶች በፕሬዚዳንትነት ወይም በምክትል ፕሬዚዳንትነት ወይም ከላይ በተገለፁ ኃላፊነቶች በውክልና የሠሩበት አገልግሎት ነው፤

11. **"አወዳዳሪ ኮሚቴ"** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሰረት የተቋቋመና በመመሪያው በተቀመጡ የመወዳደሪያ መስፈርቶች መሰረት ተወዳዳሪዎችን በመለየትና በማወዳደር ለየስራ ክፍሉ አብላጫ ውጤት በማምጣት ያሸነፉትን ለይቶ ለስራ አመራር ኮሚቴ ለውሳነ የሚያቀርብ ኮሚቴ ነው፤

12. **"የዐቃቤ ህግ አስተዳደር ጉባኤ "** ማለት የክልሉ ዐቃቢያን ህግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ እና የክልሉ ዐቃቤ ህግ አስተዳር ንዑስ ጉባኤ ፣በዞን በዐቃቢያን ህግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተዋቀሩ የዐቃቢያን ህግ አስተዳደር ንዑስ ጉባኤ ነው፤

13.በአዋጁና በደንቡ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

14.አካል ጉዳት ማለት ፤- በደረሰበት የአካል፣ የአዕምሮ ፣ወይም የስሜት ህዋሳት ጉዳት ተከትሎ የሚመጣ የኢኮኖሚ ወይም ማህበራዊ መድሎ ሳቢያ በሥራ ስምሪት የእኩል ዕድል ተጠቃሚ ያልሆነ ሰው ነው ።

## 3. ስለ ፆታ አገላለፅ

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴትም ፆታ ያገለግላል፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ፍትህ ቢሮ እና በሥር ፍትህ መዋቅሮች ዳይሬክቶሬቶች፣ጽ/ቤቶች እና የስራ ሂደቶች ላይ ለሚወዳደሩና ተወዳድረው አልፈው በሚሰሩ የስራ ክፍል ኃላፊዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 5. የመመሪያው ዓላማ

1. የሥራ ክፍል ሀላፊዎች ምድባ በውድድር ላይ ተመስርቶ ህጋዊነትን የተላበሰ፣ተጠያቂነት፣ግልፅነት፣ፍትሀዊነትና አሳታፊ በሆነ ሁኔታ የሚመራበት ስርዓት ለመዘርጋት፣
2. የሥራ ክፍል ሀላፊዎች ምደባ የተሻለ የስራ አፈፃፀምና ስነምግባር ያላቸውን ዐቃቢያነ ህግ በመለየት በመመደብ የመስሪያ ቤቱን ተልእኮ በአግባቡ እንዲፈፀም ለማስቻል፤

# ክፍል ሁለት

## ስለ ሥራ ክፍል ኃላፊዎች ምልመላና ውድድር

## 6. መርህ

**የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ምልመላና ውድድር በሚከተሉት መርሆዎች መመራት አለበት፡፡**

1. በቢሮው እና በሥር መዋቅሮቹ ያሉ እንደአዲስ የሚደራጁም ሆነ ክፍት የሥራ ክፍል ኃላፊነት ቦታዎች በሙሉ በዚህ መመሪያ መሠረት በውድድር የሚያዙ ይሆናል፤
2. የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ምልመላና ውድድር ቢሮው በህግ የተሰጠውን ስልጣን እና ተግባራት ከቢሮው መዋቅራዊ አደረጃጀት አንፃር ሊያሳካ በሚችል አግባብ በውድድር የሚከናወን ይሆናል፤
3. የባለሙያዎችን እውቀት፤ክህሎት፤ስነ-ምግባር፤ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ ከግምት ውስጥ በማስገባት፤

4. አሳታፊ እና አድሎ የሌለበት መሆን፡፡

## 7. ለየክፍሉ ኃላፊነት ውድድር የማይመለከተው ዐቃቤ ህግ

ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ ሲኖር አንድ ዐቃቤ ሕግ በክልል ደረጃ ለዳይሬክተርነት ፣ ለጽ/ቤት ኃላፊነት እና ማስተባበሪያነት እንዲሁም በዞን፣ ወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ደረጃ ለሥራ ሂደት አስተባባሪነት መወዳደር አይችልም፡-

1. በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት የተቀጣና በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የይርጋ ጊዜ ያላለፈው፤
2. በዐቃቤ ህግነት ከተቀጠረ ወይም ከተመደበ በኋላ የህግ መጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ኖሮት ፡-

   ሀ. ክልል ቢሮ ደረጃ ለመወዳደር የስራ ልምድ 8 ዓመት ያላገለገለ ፤

   ለ. በዞን ፍትህ መምሪያ ለመወዳደር የሥራ ልምድ 6 ዓመት ያላገለገለ ፣

   ሐ. በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት ለመወዳደር የስራ ልምድ 4 ዓመት ያላገለገለ፤
3. በዐቃቤ ህግነት ከተቀጠረ/ከተመደበ በኋላ በህግ 2ኛ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ኖሮት ፡-

   ሀ. ክልል ቢሮ ደረጃ ለመወዳደር የሥራ ልምድ 6 ዓመት ያላገለገለ፤

   ለ. በዞን ፍትህ መምሪያ ደረጃ ለመወዳደር የሥራ ልምድ 4 ዓመት ፣

   ሐ. በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት ለመወዳደር የሥራ ልምድ 2 ዓመት ያላገለገለ፤
4. በዐቃቤ ህግነት ከተቀጠረ/ከተመደበ በኋላ በህግ 3ኛ ዲግሪ የትምህርት ዝግጅት ኖሮት፡-

   ሀ. በክልል ቢሮ ደረጃ ለመወዳደር የሥራ ልምድ 4 ዓመት ያላገለገለ፤

   ለ. በዞን ፍትህ መምሪያ ደረጃ ለመወዳደር የሥራ ልምድ 2 ዓመት ያላገለገለ፣

   ሐ. በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት ደረጃ ለመወዳደር 1 ዓመት ያላገለገለ፤
5. በዞን ፍትህ መምሪያ ደረጃ በህግ ትምህርት ዲፕሎማ የትምህርት ዝግጅት ኖሮት በዐቃቤ ህግነት እያገለገለ ያለ ተወዳዳሪ ካለ 11 ዓመትና ከዚያ በላይ ያላገለገለ፤
6. በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ፍትሕ ጽ/ቤት ካሉት ተወዳዳሪዎች መካከል በህግ ትምህርት የዲፕሎማ የትምህርት ዝግጅት ኖሮት በዐቃቤ ህግነት እያገለገለ ያለ ተወዳዳሪ ካለ 8 ዓመትና ከዚያ በላይ ያላገለገለ፤
7. ውድድሩ በሚደረግበት ጊዜ በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ለስድስት ወራትና ከዚያ

በላይ ለሆነ ጊዜ በሚሰጥ ትምህርት ወይም ስልጠና ላይ ያሉ ዐቃቤያነ ህጎች፤

8. በዞን ፍትህ መምሪያ፣በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት ደረጃ ለመወዳደር በዐቃቤ ህግ አሰተዳደር ንዑስ ጉባኤ የተፈፀመው የዐቃቤ ህግ ቅጥር የዐቃቤ ህግ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ቅጥራቸው በክልሉ ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ቀርቦ ያልተመዘገበ እና ያልፀደቀለት ዐቃቤ ህግ በዝሁ ውድድር መሳተፍ አይችልም፡፡
9. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በፍትህ መሥሪያ ቤቶች በተለያየ ኃላፊነት ያገለገለ ከሆነ ወይም በወረዳ ደረጃ የሰው ኃይል እጥረት ያለባቸው አካባቢዎች ስሆን በሥራ ክፍል ኃላፊነት አወዳድሮ ለመመደብ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ በሚመደብበት ደረጃ ለዐቃቤ ህግ ቅጥር የሚያበቁ መስፈርቶች አሟልቶ የተቀጠረን ዐቃቤ ህግ ከላይ የተጠቀሰውን መስፈርት ባያሟሉም በልዩ ሁኔታ በውድድሩ እንዲሳተፍ ማድረግ ይቻላል፡፡

8. **የመመልመያ መስፈርት እና ክብደት**

በዚህ መመሪያ መሠረት የሚደረግ የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ምልመላና ውድድር የሚከተሉትን መስፈርትና ክብደት መነሻ አድርጎ መሆን አለበት፡-

1) የትምህርት ዝግጅት_____________30%
2) የስራ ልምድ _________________20%
3) የስራ አፈጻጸም_________________30%
4) በኃላፊ የሚሰጥ ነጥብ____________10%
5) በኃላፊነት መስራት ____________ 5 %
6) ለአካል ጉዳተኞች እና ለሴቶች የሚሰጥ ድጋፍ----------5 %

## ክፍል ሶስት

## ሥራ አመራር ኮሚቴ እና የአወዳዳሪ ኮሚቴ መቋቋም፣ተግባርና ኃላፊነት

9. **የሥራ አመራር ኮሚቴ መቋቋም**

በዚህ መመሪያ መሰረት በቢሮና በስር መዋቅር በሚገኙ የስራ ክፍሎች የሚመደቡ የስራ ሀላፊዎች ምደባን የሚያስፈፅም **"የስራ አመራር ኮሚቴ"** በዚህ መመሪያ መሰረት በተዋረድ ይቋቋማል፡፡

## 10. የሥራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

የሥራ አመራር ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡

1. አወዳዳሪ ኮሚቴውን በበላይነት ይመራል፤ይደግፋል፤ዕለት ተዕለት የሚያከናውናቸውን ተግባራት ይከታተላል፤
2. አወዳዳሪ ኮሚቴው በየስራ ክፍሉ ባሉት ክፍት የሀላፊነት ቦታዎች አወዳድሮ ያቀረበውን የአሸናፊዎች ዝርዝር መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ አስተያየት ለቢሮ ኃላፊ ያቀርባል፡፡

## 11. የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት

### 1. የፍትህ ቢሮ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት፡-

ሀ/ ቢሮ ሀላፊ________________________________________________ሰብሳቢ

ለ/ የወንጀልና ፍትሀብሄር ጉዳዮች ዘርፍ ምክትል ቢሮ ሀላፊ________________ጸሀፊ

ሐ/ የህግ ጉዳዮች ዘርፍ ምክትል ቢሮ ሀላፊ ____________________________አባል

መ/ የአስተዳደር ኮርፖረት ዘርፍ ሀላፊ______________________አባል

ሠ/ በቢሮ ሀላፊ የሚሰየም አንድ የዐቃቤ ህግ አስተዳደር ጉባኤ አባል_

### 2. የዞን ፍትህ መምሪያ የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት፡-

ሀ/ የመምሪያው ወይም የጽ/ቤቱ ሀላፊ______________________ሰብሳቢ

ለ/ በመሥሪያ ቤቱ ሀላፊ ከዐቃቢያነ ህግ ንዑስ ጉባኤ አባላት የሚሰየሙ 3 አባላት___አባል

ሐ/ በመሥሪያ ቤቱ ሀላፊ የሚሰም አንድ ዐቃቤ ህግ________________________ፀሐፊ

### 3. የወረዳ፣ የከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽ/ቤት የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት፡-

ሀ/ የጽ/ቤቱ ሀላፊ___________________________________________________ ሰብሳቢ

ለ/ በኃላፊ የሚሰየም ሁለት ዐቃቢያነ ህግ አንዱ አባል አንዱ______________ፀሐፊ

4. በዚህ አንቀፅ ከንዑስ ቁጥር 1 እስከ 3 በተዘረዘሩት የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት ውስጥ በሀላፊነት የሚወዳደር ዕጩ ካለ እርሱን የሚመለከት ጉዳይ ሲነሳ ከአባልነቱ ተነስቶ ውሳኔው በሌሎች የኮሚቴ አባላት ይሰጣል፡፡

## 12.. የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

በየደረጃው የሚገኙ የመሥሪያ ቤት ኃላፊዎች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

1. የሥራ አመራር ኮሚቴን ይሰበስባል፤ ያስተባብራል፤
2. በዚህ መመሪያ መሰረት በሀላፊ የሚሞላ አስተያየት በመሙላት ለአወዳዳሪ ኮሚቴ ያቀርባል፤
3. በአወዳዳሪው ኮሚቴ የተለዩትን አሸናፊዎች በስራ አመራር ኮሚቴ በማፀደቅ ለአሸናፊዎች የስራ ክፍል ሀላፊነት/አስተባባሪነት የምደባ ደብዳቤ እንዲደርሳቸው ያደረጋል፤
4. በስር መዋቅር በየደረጃው ያሉ የስራ ሀላፊዎች በየስራ ክፍሉ ያሸነፉትን የስራ ሀላፊዎች/አስተባባሪዎች ዝርዝር ለክልሉ ዐቃቤ ህግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ጽ/ቤት ያሳውቃል፡፡

## 13. የአወዳዳሪ ኮሚቴ መቋቋም

በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 8 በተጠቀሰው የስራ ክፍል ኃላፊዎች ምልመላና ውድድር መስፈርትና ክብደት መሰረት ከዚህ መመሪያ ጋር በአባሪነት በተያያዘው ሠንጠረዥ በተቀመጡ ዝርዝር የመመዘኛ መስፈርቶች መሰረት የቀረቡትን ማስረጃዎች በመመርመር በፍትህ ቢሮ ወይም በዞን፣በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ፍትህ መምሪያ/ፅህፈት ቤት ስር ባሉት ክፍት የስራ ክፍሎች የሚወዳደሩትን የስራ ክፍል ሀላፊዎች/አስተባባሪዎች በማወዳደር በየስራ ክፍሉ ያሸነፉትን ለይቶ ለስራ አመራር ኮሚቴ የሚያቀርብ "**አወዳዳሪ ኮሚቴ**" በዚህ መመሪያ ይቋቋሚል፡፡

## 14.የአወዳዳሪ ኮሚቴው አባላት ስብጥር

1. **የቢሮ አወዳዳሪ ኮሚቴ አባላት ስብጥር** የኮሚቴ አባላቱ የሚሰየሙት በቢሮ ሀላፊ ሆነው ከሚከተሉት የስራ ክፍሎች የተውጣጡ ይሆናሉ፡-

ሀ. ከዐቃቤ ህግ አስተዳደር ጉባኤ አባላት  የሚሰየም አንድ አባል___ሰብሳቢ፤

ለ. በስራ ልምዳቸው፣በስነምግባራቸው በሙያ ክህሎታቸው የተሻሉ ከተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚሰየሙ 3 ዐቃቤያነ ህግ____________________________አባል፤

ሐ. ከዐቃቢያነ ህግ አስተዳደር ዋ/ጉ/ጽ/ቤት የሚመደብ አንድ ዐቃቤ ህግ____አባልና  ፀሀፊ፤

2. **የዞን መምሪያ አወዳዳሪ ኮሚቴ ስብጥር** የኮሚቴው አባላት በመምሪያው ሀላፊ የሚሰየሙ ሆነው ከሚከተሉት የስራ ክፍሎች የሚውጣጡ ይሆናል፡-

ሀ. ከዐቃቤ ህግ አስተዳደር ንዑስ ጉባኤ የሚሰየም አንድ አባል_ሰብሳቢ፤

ለ. ከተለያዩ የስራ ሂደቶች በስራ ልምዳቸው፣ በስነምግባራቸው በሙያ ክህሎታቸው የተሻሉ 3 ዐቃቤያነ ህግ_______________________________አባል፤

ሐ. አንድ የሰው ሀብት አስዳደር ልማት ባለሙያ _______አባልና ፀሐፊ፤

3. የወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ፍትህ ጽህፈት ቤት አወዳዳሪ ኮሚቴ ስብጥር

የኮሚቴ አባላቱ በጽህፈት ቤት ኃላፊ የሚሰየሙ ሆነው ከሚከተሉት የስራ ክፍሎች የሚውጣጡ ይሆናል፡፡

ሀ. ከተለያዩ የስራ ሂደቶች በሥራ ልምዳቸው፣በስነምግባራቸው በሙያ ክህሎታቸው የተሻሉ 2 ዐቃቤያነ ህግ__________አንዱ ሰብሳቢ አንዱ አባል፤

ለ. አንድ የሰው ሀብት ልማትና አስተዳደር ባለሙያ ------------አባልና ፀሐፊ

4. በዚህ አንቀፅ ከንዑስ ቁጥር 1 እስከ 3 በተዘረዘሩት የአወዳዳሪ ኮሚቴ አባላት ውስጥ በኃላፊነት የሚወዳደር ዕጩ ካለ እርሱን የሚመለከት ጉዳይ ሲነሳ ከአባልነቱ ተነስቶ ውሳኔው በሌሎች የኮሚቴ አባላት ይሰጣል፡፡

15.የአወዳዳሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለቢሮ ኃላፊ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

1. ውድድሩ ግልፅ የአሠራር ሂደት የተከተለ እንዲሆን በክፍት የስራ ክፍሎች ዐቃቢያነ ህጎች እንዲወዳደሩ ለ5 ተከታታይ የስራ ቀናት የሚቆይ ግልጽ ማስታወቂያ ያወጣል፤
2. ኮሚቴው የአመልካቾችን የግል ማህደር በመመርመር በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን የውድድር ዝቅተኛ መስፈርቶችን ያሟሉ ተወዳዳሪዎችን የመለየት ስራ ይሰራል፤
3. የውድድሩን ዝቅተኛ መስፈርቶች ያሟሉትን አመልካቾች በመለየት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እንዲሁም ከዚህ መመሪያ ጋር ተያይዞ ባለው ሰንጠረዥ በተዘረዘሩት የመወዳደሪያ መስፈርቶችና ለየመስፈርቶቹ በተቀመጡ ነጥቦች መሰረት በሰንጠረዡ በተመለከተው መልኩ ነጥብ በመስጠት ውጤቱን ከመቶ (100%) ይይዛል፤
4. ኮሚቴው የተወዳዳሪው አጠቃላይ ውጤት 60 እና ከዚያ በታች የሆነ እንደሆነ ተወዳዳሪው ለሀላፊነት ብቁ አይደለም የሚል አስተያየት ጨምሮ ለውሳነ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

5. በንዑስ

6. ኮሚቴው በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት የውድድር ሥራውን ካጠናቀቀ በኋላ በውጤታቸው መሰረት አሸናፊዎቹን ለይቶ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፤

7. ኮሚቴው ለውድድር ዓላማ የሰበሰባቸውን ሰነዶች በፍትህ ቢሮ ለዐቃቤያነ ህግ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት፣በዞን፣በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ለሰው ሀብት ልማት አመራር ስራ ክፍል ይመልሳል፤

8. ሌሎች በስራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 16. ለውድድር ስለመጋበዝ

በዚህ መመሪያ መሰረት በቢሮና በስር መዋቅር ባሉ ክፍት የሀላፊነት ቦታዎች አወዳዳሪ ኮሚቴ በሚያወጣው ማስታወቂያ መሰረት በቢሮ ባሉት ክፍት የስራ ክፍሎች በቢሮ የሚሰሩ ዐቃቢያነ ህጎች፤በተዋረድ ባሉ የሀላፊነት ቦታዎች በፍትህ መምሪያ ወይም ጽህፈት ቤት ስር የሚሰሩ ዐቃቢያነ ህጎች ሁሉ የሚወዳደሩ ይሆናሉ፡፡

## 17.አወዳዳሪ ኮሚቴ ውድድሩን የሚያከናውንበት ሥርዓት

አወዳዳሪ ኮሚቴው በየደረጃው ባሉት ክፍት የስራ ክፍሎች በሚከተለው አግባብ ውድድሩን ያከናውናል፡፡

1. ተወዳዳሪው ለየስራ ክፍሉ ባቀረበው የፍላጎት መግለጫ ማመልከቻ መሰረት በመመዘኛ መስፈርቶቹ ባስመዘገበው አጠቃላይ ድምር ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ከፍተኛ ውጤት ያለው አመልካች በተወዳደረበት የስራ ክፍል አሸናፊ ይሆናል፤
2. በውድድሩ አንድን የስራ ክፍል ተመሳሳይ ምርጫቸው ያደረጉ ተወዳዳሪዎች እኩል ውጤት ያስመዘገቡ ከሆነ ኮሚቴው በሚከተለው ሁኔታ የመለየት ስራ ይሰራል፤

ሀ. ወንድና ሴት አመልካቾች ያስመዘገቡት ጠቅላላ ውጤት እኩል በሆነ ጊዜ ቅድያ ለሴት አመልካች ይሰጣል፤

ለ.ተመሳሳይ ፆታ ያላቸው አካል ጉዳተኛ ያልሆነ ተወዳዳሪና አካል ጉዳተኛ የሆነ ተወዳዳሪ ያስመዘገቡት ጠቅላላ ውጤት እኩል በሆነ ጊዜ ቅድሚያ ለአካል ጉዳተኛ ይሰጣል፤

ሐ. አካል ጉዳተኛ ወንድና አካል ጉዳተኛ ሴት ተወዳዳሪዎች ያስመዘገቡት ጠቅላላ ውጤት እኩል በሆነ ጊዜ ለአካል ጉዳተኛዋ ሴት ቅድሚያ ይሰጣል፤

መ. ሁለት ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው አካል ጉዳተኛ ተወዳዳሪዎች ወይም ሁለት አካል ጉዳተኛ ያልሆኑ ተወዳዳሪዎች ውጤታቸው ተመሳሳይ በሆነ ጊዜ አሸናፊው በሚከተለው በቅደም ተከተል ይለያል፤-

ሠ. በስራ ልምዳቸው እኩል ከሆኑ የተሻለ የትምህርት ዝግጅት ላለው ቅድሚያ ይሰጣል፤

ረ. በትምህርት ዝግጅታቸው እኩል ከሆኑ የተሻለ የመመረቂያ ነጥብ ያለው ቦታው ላይ እንዲመደብ ይደረጋል፤

ሰ. ከላይ በተጠቀሱት በሁሉም ነጥቦች እኩል ሆነው አሸናፊውን መለየት ካልተቻለ አሸናፊው በዕጣ ይለያል።

ሸ. ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ የተገለፀው ነጥብ አሰጣጥ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአካል ጉዳተኞች እና ለሴቶች የሚሰጠው ነጥብ በውድድሩ ባገኙት ነጥብ ላይ ተደምሮ ይያዝላቸዋል።

ቀ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 / ሸ / መሠረት የሚሰጠው የድጋፍ ነጥብ በውድድሩ ላይ የተሳተፈው አንድ ተወዳዳሪ ተደራራቢ የአካል ጉዳት ያለበት ከሆነ የሚሰጠው 5/አምስት/ ነጥብ በተጨማሪ ሁለት ነጥብ ይሰጠዋል።

**18. የተወዳዳሪዎች ትምህርት ማስረጃ ይዘት**

1. በውድድር ወቅት ከእያንዳንዱ ዐቃቤ ሕግ የግል ማህደር ጋር መያያዝ ያለበት የትምህርት ማስረጃ ከሀገር ውስጥ ወይም ከሀገር ውጭ ሕጋዊ እውቅና ካለው የትምህርት ተቋም የተገኘ የህግ ትምህር ዲፕሎማ ወይም የህግ የመጀመሪያ ዲግሪ/ኤል ኤል ቢ/ ወይም የህግ ሁለተኛ ዲግሪ/ኤል ኤል ኤም/ ወይም የህግ ትምህርት ሶስተኛ ዲግሪ/ፒ.ኤች.ዲ/ መሆን አለበት፣
2. በ1999 ዓመተ ምህረት እና ከዚያ በኋላ የህግ ትምህርት መማር ጀምሮ የትምህርት ማስረጃ በ2003 ዓም እና ወዲህ ያገኘ ተወዳዳሪ የመውጫ ፈተና ውጤት ማቅረብ አለበት፤

19. *የሥራ ልምድ አይነትና አያያዝ*

1. አግባብነት ያለው፣በተዘዋዋሪ አግባብነት ያለው ወይም አግባብነት የሌለው የስራ ልምድ ሲሆን አያያዙም እንደሚከተለው ይሆናል፤

ሀ. ለዐቃቤ ህግ ስራ በቀጥታ አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 9 ስር የተገለፀው የስራ ልምድ ነው፤

ለ. ለዐቃቤ ህግ ስራ በተዘዋዋሪ አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ማለት በመርማሪ ፖሊስነት ወይም በፖሊስ አዛዥነት የተሰጠ አገልግሎት ማለት ነው፤

ሐ. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ከተጠቀሱት ውጭ ያሉ የስራ ልምድ በሙሉ አግባብነት የሌለው የስራ ልምድ በሚል ይካተታል፤

2. የሥራ ልምድ አያያዝ

ሀ. ቀጥታ አግባብነት ያለው የስራ ልምድ አንድ ዓመት እንደ አንድ ዓመት ይያዛል፤

ለ. በተዘዋዋሪ አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ሶስት ዓመት እንደ አንድ ዓመት እየታጠፈ ይያዛል፤

ሐ. አግባብነት የሌለው የስራ ልምድ አራት ዓመት እንደ አንድ ዓመት እየታጠፈ ይያዛል፤

3. የተወዳዳሪው ቀጥተኛ አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ሲሰላ 9 ወር እና ከዚያ በላይ ከሆነ እንደ አንድ ዓመት ይያዛል፡፡

## 20. የሥራ ክፍል ኃላፊዎች የስራ ዘመን

1. በአንድ የስራ ክፍል ተወዳድሮ የተመደበ የስራ ክፍል ሀላፊ የስራ ዘመን የምደባ ደብዳቤ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚቆጠር አራት ዓመት ይሆናል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ የስራ ክፍል ሀላፊ የስራ ዘመን ከተጠናቀቀ በኋላ እንደማንኛውም ዐቃቤ ህግ ለቦታው እንደገና መወዳደር ይችላል፤
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰው ቢኖርም አንድ የስራ ክፍል ሀላፊ በሌላ የሥራ ክፍል ካልሆነ በስተቀር በተመሳሳይ የስራ ክፍል በሀላፊነት ከሁለት ዙር (ከስምንት ዓመት) በላይ ማገልገል አይችልም፤
4. በቀድሞ መመሪያ መሰረት ተወዳድረው የስራ ክፍል ሀላፊ የሆነ ዐቃቤ ህግ የሀላፊነት ደብዳቤ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ አራት ዓመት ሲሆናቸው የሀላፊነት ዘመናቸው ተጠናቆ በዚህ መመሪያ መሰረት የሀላፊነት ቦታው ለተወዳዳሪዎች ክፍት ይሆናል፡፡

## 21. ከኃላፊነት ስለሚነሳበት ሁኔታ

1. ማንኛውም የስራ ክፍል ሀላፊ ለሚመለከተው ሀላፊ በጽሁፍ በማሳወቅ ከሀላፊነቱ መልቀቅ ይችላል፤
2. በመስሪያ ቤቱ በሚፈጠሩት አዳዲስ የአደረጃጀትና የአሰራር ጥናት ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት አንድ የስራ ክፍል ሀላፊ በሀላፊነት እንዲመራ የተመደበበት የስራ ክፍል ከታጠፈ ወይም ከሌላ ስራ ክፍል ጋር ከተዋሀደ ከሀላፊነቱ ሊነሳ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ተወዳድሮ የተመደበ ስራ ክፍል ሀላፊ በጤና ችግር ምክንያት ወይም በአቅም ማነስ ወይም በከባድ የስነ ምግባር ችግር ምክንያት ሀላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት እንደማይችል በተጨባጭ ከተረጋገጠ በፍትህ ቢሮ ለዐቃቢያነ ህግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ቀርቦ በጉባኤው ውሳኔ፣/በዞን፣በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር በንዑስ ጉባኤ ውሳኔ ከሀላፊነት እንዲነሳ ይደረጋል፤
4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው ተወዳድረው በስራ ክፍል ሀላፊነት የተመደበ ዐቃቤ ህግ በዐቃቢያነ ህግ መተዳደሪያ ደንብ በከባድ የዲስፕሊን ጥሰትነት የተደነገገ ጥፋት ስለመፈፀሙ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ ከተረጋገጠ በየደረጃው ያሉ የመስሪያ ቤት ሀላፊዎች የስራ ክፍል ሀላፊውን ከስራ በማገድ የዲስፕሊን ክስ እንዲመሰረት ይደረጋል፤
5. በዚህ መመሪያ መሰረት በሚደረገው ውድድር የአንድ የስራ ክፍል ሀላፊ የሆነ ባለሙያ ውድድሩ ተጠናቆ የምደባ ደብዳቤ ከተሰጠው ቀን ጀምሮ ባለው ስድስት/6/ ወር ሳይሞላው በማናቸውም ሁኔታ ከሀላፊነት ከተነሳ አስቀድሞ ለቦታው በተደረገው ውድድር ከሀላፊነት ከተነሳው ወይም ቦታውን ከለቀቀ ሀላፊ ቀጥሎ ያለውን ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበ ተወዳዳሪ /ተጠባባቂ/ በቦታው እንዲመደብ የስራ አመራር ኮሚቴው ያደርጋል፡፡

22. **ከኃላፊነት የተነሱ ኃላፊዎች ስለሚመደቡበት ሁኔታ እና ስለተጠያቂነት**

1. ከሀላፊነታቸው የተነሱ የስራ ክፍል ሀላፊዎች በየመስሪያ ቤቶቻቸው ከትምህርት ዝግጅታቸውና ከስራ ልምዳቸው ጋር በሚመጥን ቦታ በዐቃቤ ህግነት እንድመደቡ ይደረጋል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ አንድ የተመለከተው ቢኖርም በከባድ የድስፕሊን ጥፋት ምክንያት ከሀላፊነታቸው የተነሱ የስራ ሀላፊዎች የወንጀልና የፍትሀብሔር

ተጠያቂነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ ዐቃቢያነ ህግ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተጠያቂ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አምስት፡

## ልዩ ልዩ ሥነ-ሥርዓታዊ ጉዳዮች

### 23. የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዐት

የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም አወዳዳሪ ኮሚቴ አከራካሪ ወይም ግልጽ ባልሆኑ ጉዳዮች የሚሰጡት ውሳኔዎች በአብላጫ ድምፅ የሚወሰኑ ሲሆን እኩል ድምፅ በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው የደገፈው አሸናፊ ይሆናል፡፡

### 24. የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዐት

1. በዚህ መመሪያ መሰረት በተደረገ ውድድር ቅሬታ አለኝ የሚል አካል በየስራ ክፍሉ ተወዳድረው ያሸነፉ የስራ ክፍል ሀላፊዎች ዝርዝር በመስሪያ ቤቱ ማስታወቂያ ቦርድ በተለጠፈ **በአምስት የስራ ቀናት** ቅሬታውን ከነምክንያቱ በየተዋረዱ ላለው የዐቃቢያነ ህግ አስተዳደር ንዑስ ጉባኤ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. ቅሬታ የቀረበለት የዐቃቢያነ ህግ አስተዳደር ንዑስ ጉባኤ የቀረበለትን ቅሬታ በ10 ቀናት ውስጥ በማጣራትና ውሳኔ በመስጠት ለቅሬታ አቅራቢው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
3. በንዑሳን ጉባኤ በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው አካል ቅሬታውን ውሳኔ በተሰጠ በ05 ቀናት ውስጥ ለቢሮ ዐቃቢያነ ህግ አስተዳደር ዋና ጉባኤ ያቀርባል፡፡ በዋና ጉባኤ የተሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

### 25. ተጠያቂነት

ይህንን መመሪያ በተዛባ መልኩ ወይም ያለአግባብ እንዲፈጸም ያደረገ ማንኛውም የኮሚቴ አባል ወይም የስራ ሀላፊ አግባብ ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 26. ተፈጻምነት የማይኖራቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ፣ ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 27.መመሪያውን ስለማሻሻል

የክልሉ ፍትህ ቢሮ መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 28. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ከጸደቀበት ከ24/1/2017 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አበነዘር ተረፈ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት**

**የፍትህ ቢሮ ኃላፊ**

መስከረም 24/2017 ዓ/ም

**ሳውላ**

## አባሪ ሰንጠረዥ 1.

**የትምህርት ዝግጅት ከ30 የሚያስገኛው ውጤት/በሁሉም ደረጃ ለሚደረግ ውድድር/**

| ተ.ቁ | መለኪያ | ነጥብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|
| 1 | **የትምህርት ዝግጅት አያያዝ/በሁሉም ደረጃ ለሚደረግ ውድድር/** | **ከ30** | |
| | • በህግ ትምህርት ዘርፍ ሶስተኛ ዲግሪ/ፒ.ኤች ዲ/ ያለው/ያላት | 30 | |
| | • በህግ ትምህርት ዘርፍ የሁለተኛ ዲግሪ/ኤል.ኤል.ኤም/ ያለው/ያላት | 27 | |
| | • በህግ ትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪ/ኤል.ኤል.ቢ/ያለው/ያላት | 24 | |
| | • በህግ ትምህርት ዲፕሎማ ያላቸው | 21 | |

**የሁለት ተከታታይ ሚዘና ጊዜያት የውጤት ተኮር ዕቅድ አፈፃፀም አማካይ ውጤት ከ30 የሚያስገኛው ነጥብ/በሁሉም ደረጃ ለሚደረግ ውድድር/**

| ተራ ቁጥር | ተወዳዳሪው አማካይ የስራ አፈፃፀም ውጤት | ከ30 የሚያስገኛው ነጥብ | ምር መራ |
|---|---|---|---|
| | 95 እና ከዚያ በላይ | 30 | |
| | 94 እስከ 94.99 | 29.5 | |
| | 93 እስከ 93.99 | 29 | |
| | 92 እስከ 92.99 | 28.5 | |
| | 91 እስከ 91.99 | 28 | |
| | 90 እስከ 90.99 | 27.5 | |
| | 89 እስከ 89.99 | 27 | |
| | 88 እስከ 88.99 | 26.5 | |
| | 87 እስከ 87.99 | 26 | |
| | 86 እስከ 86.99 | 25.5 | |
| | 85 እስከ 85.99 | 25 | |
| | 84 እስከ 84.99 | 24.5 | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | 83 እስከ 83.99 | 24 | |
| | 82 እስከ 82.99 | 23.5 | |
| | 81 እስከ 81.99 | 23 | |
| | 80 እስከ 80.99 | 22.5 | |
| | 79 እስከ 79.99 | 22 | |
| | 78 እስከ 78.99 | 21.5 | |
| | 77 እስከ 77.99 | 21 | |
| | 76 እስከ 76.99 | 20.5 | |
| | 75 እስከ 75.99 | 20 | |
| | 74 እስከ 74.99 | 19.5 | |
| | 73 እስከ 73.99 | 19 | |
| | 72 እስከ 72.99 | 18.5 | |
| | 71 እስከ 71.99 | 18 | |
| | 70 እስከ 70.99 | 17.5 | |
| | 69 እስከ 69.99 | 17 | |
| | 68 እስከ 68.99 | 16.5 | |
| | 67 እስከ 67.99 | 16 | |
| | 66 እስከ 66.99 | 15.5 | |
| | 65 እስከ 65.99 | 15 | |
| | 64 እስከ 64.99 | 14.5 | |
| | 63 እስከ 63.99 | 14 | |
| | 62 እስከ 62.99 | 13.5 | |
| | 61 እስከ 61.99 | 13 | |
| | 60 እስከ 60.99 | 12..5 | |
| **በሀላፊነት ያገለገሉት አገልግሎት ከ5 ነጥብ የሚያስገኛው ውጤት/በሁሉም ደረጃ ለሚደረግ ውድድር/** | | | |
| 1. | 10 ዓመትና ከዚያ በላይ | 5 | |
| 2. | ከ9 እስከ 9 ዓመት ከ11ወር | 4 | |
| 3. | ከ8 እስከ 8 ዓመት ከ11ወር | 3 | |
| 4. | ከ7 እስከ 7 ዓመት ከ11ወር | 2.5 | |
| 5. | 6 እስከ 6 ዓመት ከ11ወር | 2 | |
| 6. | 5 እስከ 5ዓመት ከ11ወር | 1.05 | |
| 7. | 4 እስከ 4 ዓመት ከ11ወር | 1 | |
| 8. | 3 እስከ 3 ዓመት ከ11ወር | 0.75 | |
| 9. | 2 እስከ 2 ዓመት ከ11ወር | 0.5 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 10. | 1 እስከ 1 ዓመት ከ11ወር | 0.5 | | |
| **በሀላፊ የሚሰጥ ነጥብ 10%/በሁሉም ደረጃ ለሚደረግ ውድድር/** | | | | |
| | መስፈርቶች | ከ10 የሚይዘው ነጥብ | ምርመራ | |
| 1. | ዐቃቤ ህጉ የተቋሙን ራዕይና ተልእኮ በአግባቡ ተረድቶ የመስራት፤ | 2 | | |
| 2. | ዐቃቤ ህጉ ያለው ሙያዊ ብቃት፣እውቀትና ክህሎት፤ | 2 | | |
| 3. | ዐቃቤ ህጉ ያለው የማስፈፀም፣ የማቀድ፣ የመምራት፣ የማስተባበርና የመቆጣጠር ብቃት፤ | 2 | | |
| 4. | ዐቃቤ ህጉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የተቋሙን ስራ በቴክኖሎጂ በማስደገፍ የመስራት ብቃት | 1 | | |
| 5. | ዐቃቤ ህጉ ስራን በራሱ ተነሳሽነት የመስራትና የስራ ግዜን በአግባቡ የመጠቀም ብቃት | 1 | | |
| 6. | ዐቃቤ ህጉ ሀላፊነትን ለመቀበል ያለው ዝግጁነት | 2 | | |

## በክልል ፍትህ ቢሮ ደረጃ ለሚደረግ ውድድር ለስራ ልምድ ከ20 የሚያዝ ውጤት

| | በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ/LL.B/ያለው/ያላት | በህግ ሁለተኛ ዲግሪ/LL.M/ያለው/ያላት | በህግ ሶስተኛ ዲግሪ/PhDያለው/ያላት | ነጥብ ከ 20 |
|---|---|---|---|---|
| 1. | 17 ዓመትና ከዚያ በላይ | 15 ዓመትና ከዚያ በላይ | 13 ዓመትና ከዚያ በላይ | 20 |
| 2. | 16 ዓመት ከ1ወር እስከ 16 ዓመት ከ11 ወር | 14ዓመት ከ1ወር እስከ 14 ዓመት ከ11 ወር | 12 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 19 |
| 3. | 15 ዓመት ከ1ወር እስከ 15 ዓመት ከ11 ወር | 13ዓመት ከ1ወር እስከ 13 ዓመት ከ11 ወር | 11 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 18 |
| 4. | 14 ዓመት ከ1ወር እስከ 14ዓመት ከ11 ወር | 12ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 10 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 17 |
| 5. | 13 ዓመት ከ1ወር እስከ 13 ዓመት ከ11 ወር | 11ዓመት ከ1ወር እስከ 11 ዓመት ከ11 ወር | 9 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 16 |
| 6. | 12 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 10ዓመት ከ1ወር እስከ 10 ዓመት ከ11 ወር | 8 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 15 |
| 7. | 11 ዓመት ከ1ወር እስከ 11ዓመት ከ11 ወር | 9ዓመት ከ1ወር እስከ 9ዓመት ከ11 ወር | 7 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 14 |
| 8. | 10 ዓመት ከ1ወር እስከ 10 ዓመት ከ11 ወር | 8ዓመት ከ1ወር እስከ 8 ዓመት ከ11 ወር | 6 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 13 |
| 9. | 9 ዓመት ከ1ወር እስከ 9 ዓመት ከ11 ወር | 7ዓመት ከ1ወር እስከ 7 ዓመት ከ11 ወር | 5 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 12 |
| 10 | 8 ዓመት ከ1ወር እስከ 8 ዓመት ከ11 ወር | 6 ዓመት ከ1ወር እስከ 6 ዓመት ከ11 ወር | 4 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 11 |

**በዞን በሚሰሩ ዓቃቢያነ ህግ መካከል ለህላፊነት በሚደረግ ውድድር ለስራ ልምድ ከ20 የሚያዝ ነጥብ**

| | በህግ ትምህርት ዲፕሎማ ያለው/ያላት | በህግ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ/LL.B/ ያለው/ያላት | በህግ ትምህርት ሁለተኛ ዲግሪ/LL.M/ ያለው/ያላት | በህግ ትምህርት ሶስተኛ ዲግሪ/PhD/ ያለው/ያላት | ነጥብ ከ 20 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | 20 ዓመትና ከዚያ በላይ | 15 ዓመት ዓመትና ከዚያ በላይ | 13 ዓመት እና ከዚያ በላይ | 11 ዓመት እና ከዚያ በላይ | 20 |
| 2. | 19 ዓመት ከ1ወር እስከ 19 ዓመት ከ11 ወር | 14 ዓመት ከ1ወር እስከ 14 ዓመት ከ11 ወር | 12 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 10 ዓመት እና ከዚያ በላይ | 19 |
| 3. | 18 ዓመት ከ1ወር እስከ 18 ዓመት ከ11 ወር | 13 ዓመት ከ1ወር እስከ 13 ዓመት ከ11 ወር | 11 ዓመት ከ1ወር እስከ 11 ዓመት ከ11 ወር | 9 ዓመት ከ1ወር እስከ 9 ዓመት ከ11 ወር | 18 |
| 4. | 17 ዓመት ከ1ወር እስከ 17 ዓመት ከ11 ወር | 12 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 10 ዓመት ከ1ወር እስከ 10 ዓመት ከ11 ወር | 8 ዓመት ከ1ወር እስከ 8 ዓመት ከ11 ወር | 17 |
| 5. | 16 ዓመት ከ1ወር እስከ 16 ዓመት ከ11 ወር | 11 ዓመት ከ1ወር እስከ 11 ዓመት ከ11 ወር | 9 ዓመት ከ1ወር እስከ 9 ዓመት ከ11 ወር | 7 ዓመት ከ1ወር እስከ 7 ዓመት ከ11 ወር | 16 |
| 6. | 15 ዓመት ከ1ወር እስከ 15 ዓመት ከ11 ወር | 10 ዓመት ከ1ወር እስከ 10 ዓመት ከ11 ወር | 8 ዓመት ከ1ወር እስከ 8 ዓመት ከ11 ወር | 6 ዓመት ከ1ወር እስከ 6 ዓመት ከ11 ወር | 15 |
| 7. | 14 ዓመት ከ1ወር እስከ 14 ዓመት ከ11 ወር | 9 ዓመት ከ1ወር እስከ 9 ዓመት ከ11 ወር | 7 ዓመት ከ1ወር እስከ 7 ዓመት ከ11 ወር | 5 ዓመት ከ1ወር እስከ 5 ዓመት ከ11 ወር | 14 |
| 8. | 13 ዓመት ከ1ወር እስከ 13 ዓመት ከ11 ወር | 8 ዓመት ከ1ወር እስከ 8 ዓመት ከ11 ወር | 6 ዓመት ከ1ወር እስከ 6 ዓመት ከ11 ወር | 4 ዓመት ከ1ወር እስከ 4 ዓመት ከ11 ወር | 13 |
| 9. | 12 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 7 ዓመት ከ1ወር እስከ 7 ዓመት ከ11 ወር | 5 ዓመት ከ1ወር እስከ 5 ዓመት ከ11 ወር | 3 ዓመት ከ1ወር እስከ 3 ዓመት ከ11 ወር | 12 |
| 10. | 11 ዓመት ከ1ወር እስከ 11 ዓመት ከ11 ወር | 6 ዓመት ከ1ወር እስከ 6 ዓመት ከ11 ወር | 4 ዓመት ከ1ወር እስከ 4 ዓመት ከ11 ወር | 2 ዓመት ከ1ወር እስከ 2 ዓመት ከ11 ወር | 11 |

**በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር ደረጃ በሚሰሩ ዐቃቢያነ ህግ ለስራ ክፍል ሀላፊነት ለሚደረግ ውድድር ለስራ ልምድ ከ20 የሚያዝ ውጤት**

| | በህግ ትምህርት ዲፐሎማ ያለው/ያላት | በህግ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ/LL.B/ ያለው/ያላት | በህግ ትምህርት ሁለተኛ ዲግሪ/LL.M/ ያለው/ያላት | በህግ ትምህርት ሶስተኛ ዲግሪ/PhD/ ያለው/ያላት | ነጥብ ከ 20 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | 17 ዓመትና ከዚያ በላይ | 13 ዓመትና ከዚያ በላይ | 11 ዓመትና ከዚያ በላይ | 9 ዓመትና ከዚያ በላይ | 20 |
| 2. | 16 ዓመት ከ1ወር እስከ 16 ዓመት ከ11 ወር | 12 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 10 ዓመት ከ1ወር እስከ 11 ዓመት ከ11 ወር | 8ዓመት ከ1ወር እስከ 8 ዓመት ከ11 ወር | 19 |
| 3. | 15 ዓመት ከ1ወር እስከ 15 ዓመት ከ11 ወር | 11 ዓመት ከ1ወር እስከ 11 ዓመት ከ11 ወር | 9 ዓመት ከ1ወር እስከ 9 ዓመት ከ11 ወር | 7 ዓመት ከ1ወር እስከ 7 ዓመት ከ11 ወር | 18 |
| 4. | 14 ዓመት ከ1ወር እስከ 14 ዓመት ከ11 ወር | 10 ዓመት ከ1ወር እስከ 10 ዓመት ከ11 ወር | 8ዓመት ከ1ወር እስከ 8 ዓመት ከ11 ወር | 6 ዓመት ከ1ወር እስከ 6 ዓመት ከ11 ወር | 17 |
| 5. | 13 ዓመት ከ1ወር እስከ 13 ዓመት ከ11 ወር | 9 ዓመት ከ1ወር እስከ 9 ዓመት ከ11 ወር | 7 ዓመት ከ1ወር እስከ 7 ዓመት ከ11 ወር | 5 ዓመት ከ1ወር እስከ 5 ዓመት ከ11 ወር | 16 |
| 6. | 12 ዓመት ከ1ወር እስከ 12 ዓመት ከ11 ወር | 8 ዓመት ከ1ወር እስከ 8 ዓመት ከ11 ወር | 6 ዓመት ከ1ወር እስከ 6 ዓመት ከ11 ወር | 4 ዓመት ከ1ወር እስከ 4 ዓመት ከ11 ወር | 15 |
| 7. | 11 ዓመት ከ1ወር እስከ 11ዓመት ከ11 ወር | 7ዓመት ከ1ወር እስከ 7 ዓመት ከ11 ወር | 5 ዓመት ከ1ወር እስከ 5 ዓመት ከ11 ወር | 3 ዓመት ከ1ወር እስከ 3 ዓመት ከ11 ወር | 14 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 8. | 10 ዓመት ከ1ወር እስከ 10 ዓመት ከ11 ወር | 6 ዓመት ከ1ወር እስከ 6 ዓመት ከ11 ወር | 4 ዓመት ከ1ወር እስከ 4 ዓመት ከ11 ወር | 2 ዓመት ከ1ወር እስከ 2 ዓመት ከ11 ወር | 13 |
| 9. | 9 ዓመት ከ1ወር እስከ 9 ዓመት ከ11 ወር | 5 ዓመት ከ1ወር እስከ 5 ዓመት ከ11 ወር | 3 ዓመት ከ1ወር እስከ 3 ዓመት ከ11 ወር | 1 ዓመት ከ1ወር እስከ ዓመት ከ11 ወር | 12 |
| 10. | 8 ዓመት ከ1ወር እስከ 8 ዓመት ከ11 ወር | 4ዓመት ከ1ወር እስከ 4 ዓመት ከ11 ወር | 2 ዓመት ከ1ወር እስከ 2 ዓመት ከ11 ወር | 0 ዓመት ልምድ ያለው | 11 |